ለ -----------------------------------------------------------

<u>አዲስ አበባ፣</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመጽሐፍ ማሳተሚያ ድጋፍ(Sponsor ship) ጥያቄ፡-</u>

<u>**ድጋፍ ጠያቂ፡-**</u> እኔ ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር ላለፉት ሠላሳ ስድስት ዓመታት በመምህርነት፣ በርእሰ መምህርነት፣ በጋዜጠኛነት (በመንግሥትና በግል) ከማገልገሌም በላይ ከ1986 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የፈለገ ጥበብ መጽሔት ዋና አዘጋጅና የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ከፍተኛ ሪፖርተር በመሆን በመሥራት ላይ እገኛለሁ።

ከዚህም በላይ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ሬዲዮ እሑዱ መዝናኛ ፕሮግራም፣በቅርቡ ደግሞ በሸገር ኤፍ ኤም 102.1 እና በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን በኤፍ ኤም 97.1 የራሴ ፕሮግራም በመክፈት ሠርቻለሁ።

መጻሕፍትን በተመለከተ ባህላዊ፣ ትውፊታዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው፡-

1. ኀብረ ብዕር 1ኛ መጽሐፍ
2. .. .. 2ኛ መጽሐፍ
3. ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትላንትና

የተሰኙትን አሳትሜ ለንባብ አብቅቻለሁ። አሁን ደግሞ በወቅታዊነቱ ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊያበረክት የሚችል **"ሀገር በቀል ዕፅዋት ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ባህል አንጻር"** የሚል መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ። ይሁንና አሁን ካለው የኅትመት ዋጋ ውድነት የተነሣ መጽሐፉን ለማሳተም ከአቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ትብብርዎን ለመጠየቅ ተገድጃለሁ። በዚህ አጋጣሚ ለሚደረግልኝ ድጋፍ ሁሉ አስቀድሜ ምስጋናዬን እያቀረብኩ የመጽሐፉን ይዘት የሚገልጽ ጠቃሚ ማብራሪያ 3ገጽ ከዚህ ማመልከቻ ጋር በአባሪነት ማቅረቤን በትሕትና እገልጻለን።

ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር

0911 13 34 37

**የመጽሐፉ ስም (ርእስ)**፡-‹‹ሀገር በቀል ዕፅዋት ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ባህል አንጻር››

**የገጽ ብዛት፡-** 160

**መግቢያ፡-**

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በብሪቲሽ ካውንስል ትብብር ተዘጋጅቶ በነበረው የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ባተኮረ ዐውደ ጥናት ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕፅዋትን የምትንከባከበው ለምንድን ነው?›› በሚል ርእስ አቅርቤው የነበረው ጥናታዊ ጽሑፍ መነሻ አድርጌ ያዘጋጀሁት ነው ።

ጥናታዊ ጽሑፉ ካለው ጠቀሜታና ከተሳታፊዎች በቀረበው ሐሳብ መሠረት በቀጣይነትም መጠነኛ መሻሻልና ለውጥ ተደርጎበት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ አዘጋጅቶት በነበረው ሀገር አቀፍ የሰባኪያነ ወንጌል የአቅም ግንባታ ዐውደ ጥናት ቀርቦ ነበር ። የሁለቱም ዐውደ ጥናቶች ተሳታፊዎች ‹‹ጥናታዊ ጽሑፉ ሰፋ ባለ ሁኔታ በመጽሐፍ መልክ ቢዘጋጅ ለሰባኪያነ ወንጌልና ካህናት የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ ሕዝቡን ለማስተማር እንደ አጋዥ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግላቸው ችላል›› በማለት ለደራሲውና ለሁለቱም መምሪያዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ ።

**ዓላማ፡-**

1. ኢትዮጵያውን ዕፀዋትን በመንከባከብ፣ በዕፀዋት በመጠቀምና ሌሎችን ስለዕፀዋት በማስተማር የረዥም ዘመናት ታሪክ እንዳላቸው ለማሳወቅ ።
2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕፀዋትን የምትንከባከብባቸው መሠረታዊ መንስኤዎችና ምክንያቶችን ለማሳወቅ ብሎም አሁን ዕፀዋትን በመንከባከብ በኩል እየታየ ያለውን ድክመነት ለማረም የሚያስችል ግንዛቤ ለመፍጠር ።
3. ሀገር በቀል ዛፎች ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጋር ያላቸው ትስስር ከመኖርና ካለመኖር ህልውና ጋር የተያያዘ መሆኑን ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲረዳ ለማድረግ ።
4. ሀገር በቀል ዛፎች ከሚያበረክቱት ሁለገብ ጠቀሜታ ባሻገር በባህል፣ በእምነትና ሕክምና ዘርፎች ባላቸው አስተዋጽኦ ዙሪያ ምርምርና ጥናት ማካሔድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች መነሻ የሚሆን ዕውቀት ለማስጨበጥ ።
5. ዕፀዋትና የአየር ንብረት ለውጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ ምን እንደሚመስል አጉልቶ በማሳየት ሕዝበ ክርስቲያኑ የአየር ንብረት ብክለት ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ለማነሳሳት የሚያስችል ግንዛቤ ለመስጠት ።

## የመጽሐፉ ይዘት

**ምዕራፍ 1፡-**

መግቢያ

- ዕፀዋትና ኢትዮጵያውያን እንደ መነሻ፤

**ምዕራፍ 2**

ዕፀዋት በመጽሐፍ ቅዱስ

- የንጽጽርና የጸሎት ቅመም በመሆን፤
- ዕፀዋት እንደተምሳሌቶች
- የሀገርና የቦታ ተምሳሌት በመሆን፤
- ዕፀዋትን በተመለከተ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ትእዛዛት፤
- ዕፀዋት በጥበብ ተምሳሌት፤

**ምዕራፍ 3፡-**

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕፀዋትን የምትንከባከበው ለምንድን ነው?

- ዕፀዋት ለመጠለያና ለሕንፃ ሥራ ወሳኝ መሆናቸው፤
- ዕፀዋት የንዋያተ ቅድሳት ምንጭ መሆናቸው፤
- ዕፀዋት ለቤትና ለቁሳቁሶች መሥሪያ ማገልገላቸው፤
- ዕፀዋት እንደ ምግብ (ክፍል 1)
- ዕፀዋት በትምህርት አጋዥነታቸው፤
- ኢትዮጵያውያን፣ ሊቃውንትና ዕፀዋት፤
- ከዕፀዋት ጋር በተያያዘ የቀረቡ ቅኔያት፤

**ምዕራፍ 4፡-**

የዕፀዋት ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዙሪያ፤

- የበዓላት አከባበርና የዕፀዋት ድርሻ፤
- ዕፀዋት እንደ ምግብ (ክፍል 2)
- ዕፀዋት እንደ መድኃኒት (ለሰው)
- ዕፀዋት እንደ መድኃኒት (ለእንስሳ)
- ዕፀዋት እንደ መድኃኒት (ለአዝርእት)
- ዕፀዋት እንደ መጠጥ (ከሳው)
- ዕፀዋት በንጽሕና መጠበቅያነት፤
- ዕፀዋት እንደ ፍርድ ሸንጎና አደባባይ፤
- ዕፀዋት እንደ በትርና ዱላ፤

- ዕፀዋትና የአካላዊ ብቃት (ስፖርት) እንቅስቃሴ፤
- ዕፀዋትና ሥነ ቃል፤
- ዕፀዋት ለወታደራዊ አገልግሎት፤
- ዕፀዋት ለመዋቢያነትና ለመልካም መዓዛ
- ዕፀዋትና ፆታ

**ምዕራፍ 5፡-**

ዕፀዋትና የአየር ንብረት ለውጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ

- የአየር ንብረት ለውጥ እንዴትና ለምን ተጀመረ?
- በሰው ጥፋት ምክንያት የተከሰቱ ዐበይት የዓየር ንብረት ለውጦች፤
- የሰው ጥፋትና የእግዚአብሔር ትዕግስት፤
- የእግዚአብሔር ቅጣትና የአየር ንብረት ለውጥ፤
- የአየር ንብረት ከመመረቅና መረገም አንጻር፤
- የአየር ንብረት ለውጥ በአሁኑ ጊዜ፤
- የአየር ንብረት ለውጥና ሃይማኖታዊ መፍትሔዎች
- ሀገር በቀል ዕፀዋት ለአየር ንብረት መስተካከል ያላቸው ድርሻ፤

**ምዕራፍ 6፡-**

- አሁን በዕፀዋት ውድመትና በአየር ንብረት ለውጥ እየታዩ ያሉትን ግድፈቶች ለማረም ምን መደረግ አለበት?
- ማጠቃለያ